

# ሰማይ

ዮሐንስ በራዕይ መፅሐፍ “አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ፤ ቅድስቲቱን ከተማ አዲሲቱን ኢየሩሳሌምንም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።” ብሎ ፃፈ።

መልአኩም ለዮሐንስ የሚከተሉትን ቃላት ነገረው። “እነሆ በቶሎ እመጣለሁ! ሽልማት ይዤ እመጣለሁ። ለእያንዳንዱ ሰውም እንደስራው እከፍለዋለሁ። እኔ ከሁሉም ነገሮች በፊት ነበርኩ። ደግሞም እኔ መጨረሻ ነኝ። የሚታዘዙኝ ይባረካሉ። ከሕይወት ዛፍ ይበላሉ። በቅድስቲቱ ሰማያዊት ከተማም በር ይገባሉ።”

የመፅሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው መፅሐፍ ስለዚህች ውብ ከተማ ያወራል። ስለዚህች ከተማ ሲናገርም በወርቅ የተሰራች እጅግ ትልቅ ከተማ እንደሆነች ይናገራል። አስራ ሁለቱ የከተማዋ መሰረቶችም በተለያዩ የከበሩ ድንጋዮች እንዳጌጡ ይናገራል። ይህች ከተማ አስራ ሁለት በሮች ሲኖሯት እያንዳንዱ በርም ከግዙፍ እንቁ የተሠራ ነበር። የአስራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ስም በበሮቹ ላይ ተፅፈው ነበር። በሮቹም ሁልጊዜ ክፍት ናቸው፤ በፍፁም አይዘጉም። የከተማይቱ ጎዳናም ልክ እንደመስታወት በሚያንፀባርቅ ወርቅ የተሰራ ነበር። በዚያ ፀሐይም የለም ጨረቃም የለችም። የእግዚአብሔርና የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ለከተማይቱ ብርሃን ነበሩ። . ከተማይቱን ጨለማ በፍፁም አያውቃትም ።

በከተማይቱ ውስጥ የነበረው ነገር በሙሉ ንፁህ ነበር። ምክንያቱም ንፁህ ያልሆነ ነገር ወደከተማይቱ ሊገባ አይችልምና ነው። በከተማይቱ ውስጥ ለቅሶም ሆነ ሀዘን ፈፅሞ አይታወቅም። ምንኛ ደስ የሚል ስፍራ ነው!

ኢየሱስ እንዲህ አለ “ እነኝህን ነገሮች እንዲነግርህ መልአኬን ልኬያለሁ። እኔ የሚያበራ የንጋት ኮከብ ነኝ። አዎ! በቶሎ እመጣለሁ።”

*ስለመንግስተ ሰማይ ስዕላዊ መግለጫ በመጨረሻው የመፅሐፍ ቅዱስ መፅሐፍ በራዕይ ምዕራፍ 21 እና ምዕራፍ 22 ላይ እናገኛለን።።*

http://gardenofpraise.com